# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

ቁጥር 232 ጥቅምት 15 2005 ገጽ 1

ዘንድሮም በጨነገፉ መንግሥታት መለኪያ ዓለምን የምትመራው ጎረቤታችን ሶማሊያ ስትሆን ያገኘችው አጠቃላይ ነጥብ 114.9 ነው። ኢትዮጵያ በ97.9 በሆነ አጠቃላይ ነጥብ 17ኛ ደረጃ ይዛ በቅርብ እርቀት ትከተላታለች። ለማነፃፀር ያህል ዩጋንዳ፣ ስሪላንካ፣ ብሩንዲ፣ ላይቤሪያ፣ ሩዋንዳ እና ኤርትራ ከኢትዮጵያ የተሻለ አስተማማኝ መንግሥታት ያላቸው ሆነው ተገኝተዋል። እስከ ሠላሳ ሶስተኛ ተራ ቁጥር የተዘረዘሩት መንግሥታት "በመውደቅ ላይ ያሉ መንግሥታት" የሚል ስያሜ ተሰጥቷቸዋል።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የዘንድሮው ኢድ አል አደሃ በአል የሙስሊሙ ህብረተሰብ ተቃውሞ መግለጫ ሆኖ አለፈ

በመላው ኢትዮጵያ በሚገኙ ትላልቅ ከተሞች ትናንት ለ1433ኛ ጊዜ ተከብሮ በዋለው የኢዷ አል አደሃ በአል ላይ የተገኘው ቁጥሩ በብዙ መቶ ሺ የሚቆጠር ህዝብ ወያኔ በሙስሊም እምነት ውስጥ የሚያካህደውን ጣልቃ ገብነት እንዲያቆምና ባለፈው ሳምንት በየቀበለው የተደረገው ምርጫ ህጋዊነት እንደሌለው በመግለጽ የተለያዩ የተቃውሞ መፈክሮች ሲስተጋቡበት መዋሉን ለማረጋገጥ ተችሎአል።

በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የሚገኘው የታላቁ የአንዋር መስጊድ አሰጋጅ የሆኑት ሼህ ጠሀ ሞሀመድ ሀሩን ምእመናን ምንም አይነት ተቃውሞ ሳያሰሙ ሰግደው በሰላም ወደየበታቸው እንዲሄዱ በመጠየቃቸው ወደ ተቃውሞ መግለጫነት የተቀየረው የአዲስ አበባው የበአል ሥነሥራአት በህበረተሰቡ ዘንድ እንዳይታወቅ ወያኔ ቁጥጥር ሥር የሚተዳደረው የኢትዮጵያ ቴለቪዥን በምስል የተደገፈ ምንም አይነት የዘገባ ሽፋን እንዳልሰጠው ታውቆአል። የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ግን ህዝቡ ያሰማውን ተቃውሞ በመደበቅ በአሉ በታላቅ ድምቀት እንደተከበረና ለድምቀቱም ዋናው ምክንያት በቅርቡ የእስልምና እምነት ተከታዮች ያካሄዱት የሃይማኖት መሪዎች ምርጫ በሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ መንገድ መጠናቀቁ እንደሆነ በመግለጹ የህዝብ ትዝብት አትርፎአል።

በአዲስ አበባ ስታዲዬም በተከናወነው የኢድ አል አደሃ በአል ላይ የተቃውሞ መፈክር ያሰማው የአዲስ አበባ ምዕመናን "መንግሥት የለም ወይ መንግሥት የለም ወይ በማለት ሥልጣን ላይ ያለው አገዛዝ መብታቸውን እንዳላስጠበቀ ሲገልጹ የኢትዮጵያ ቴለቪዥንንና በወያኔ ሞግዚትነት ሥር የሚተዳደረውን መጅሊስ ሥም እየጠሩ ሌባ ሌባ ሲሉ ተደምጠዋል። (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## ወያኔ/ኢህአደግ ውስጥ የተፈጠረው ክፍፍል ግንባሩን ከማዳከም አልፎ ወደ መግደል እያመራ መሆኑን የወያኔ ልሳን የሆነው ሪፖርተር አስጠነቀቀ

የህወሃት የቀድሞ ታጋይና በመጀመሪያዎቹ የወያኔ አገዛዝ የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴለቪዥንን መሥሪያቤትን ለረጅም ጊዜ በሃላፊነት ሲመራ የቆየው አማረ አረጋዊ ንብረት የሆነው ሪፖርተር ጋዜጣ ባለፈው ረቡዕ ር ዕሰ አንንቀጹ እንዳሰፈረው ህዝብ በሃዘን ወቅት ስላዘነና በደስታም ጊዜ በጋራ ስለ ጨፈረ ከወያኔ / ኢህአዴግ ጋር ያለውን ግንኙነት በአወንታዊ መልኩ አንጸባረቀ ማለት አለመሆኑንና ይልቁኑም በበርካታ ችግሮች ምክንያት ልቡ ከድርጅቱ መራቁን በመግለጽ የቀድሞ ጓዶቹ ሳይመሽባቸው መልሰው የሚጠናከሩበትን ዜዴ አጥብቀው እንዲሹ አሳስቦአል።

ወያኔ ዛሬም እንደ ትናንቱ ጠንካራ ነኝ እያለ ራሱንና አንዳንድ የዋሆችን ለማታለል ቢሞክርም እውነታው ግን ፍጹም የተለየና በሌላ ጽንፍ ያለ መሆኑ ያሳሰበው ሪፖርተር ወያኔ / ኢህአዴግ ደፋርና ቆራጥ የውስጥ ትግል አካሂዶ ካልተስተካከለ በስተቀር በስብሶ መደርመሱና የነበረው እንዳልነበረ መሆኑ አይቀርም በማለት አስጠንቅቆአል።

ሪፖርተር የቀድሞ የትግል ጓዶቹንና እስከ ደርግ መውደቅ የታገለለትን ፓርቲውን ከውድቀት ለማዳን ተጨንቆ በጻፈው በዚህ ርዕሰ አንቀጽ በእርግጥ ከተቃዋሚዎች አንጻር ሲታይ ግንባሩ የተሻለ አንድነት ቢኖረውም ወቅቱ ከሚጠይቀው አኳያ ግን የውስጥ አንድነቱ ደካማ ስለሆነ ይህንን እውነታ ከግንዛቤ በማስገባት እራስን ከማታለል ተቆጥቦ የቀድሞ አንድነትን በቶሎ መመለስ የተገባ ነው ብሎአል።

ሪፖርተር አንድነቱን በመጠበቅ ከተቃዋሚው ይሻላል በማለት ለማወደስ የሞከረውን ፓርቲ ዞር ብሎ ደግሞ አራቱም የኢህአዴግ ድርጅቶች ማለትም ህወሃት፣ ብአዴን፣ ኦህዴድና ደህዴን በየውስጣቸውም ሆነ እርስ በእርሳቸው ባላቸው ግንኙነት አንድነት የላቸውም፤ የተሻለ አንድነት የነበረው ህወሃት እንኳን ያ አንድነቱ ዛሬ በውስጡ የለም በማለት የመለስን ሞት ተከትሎ ወያኔ ኢህአደግ ውስጥ የተፈጠረው (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

ግዜ ግንቦት 7 ዜና

## ኢትዮጵያ ዉስጥ ለተፈጠረዉ ከፍተኛ የቁጠባ እጥረት ዋናዉ ምክንያት የህወሀት አባላት ንብረት የሆኑት የንግድ ባንኮች መሆናቸዉ ታወቀ

ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ ከህዝብ የሚቀርብበትን ከፍተኛ ተቃዉሞ አቅጣጫ ለማስቀየር ሲል ያለምንም በቂ ጥናትና ዝግጅት ከአቅሙ በላይ እዚህና እዚያ ያስቀመጣቸው ፕሮጀክቶች የአገሪቱን የካፒታል ጥሪት እንዳራቆተ በግልጽ የሚታወቅ ቢሆንም ከዚህ በተጨማሪ ዛሬ ኢትዮጵያ ዉስጥ ለሚታየዉ የቁጠባ ካፒታል እጥረት በዋና ምክንያትነት ሊጠቀሱ የሚችሉት በህወሀት ባለስልጣኖች ቁጥጥር ስር የሚገኙት የግል ንግድ ባንኮች ናቸዉ ሲሉ አንድ ስማቸዉ እንዳይጠቀስ የፈለጉ ምሁር ገለጹ።

እኚህ በኢትዮጵያ የፋይናንስ ዘርፍ ላይ ሰፋ ያለ ጥናት ያካሄዱት የኤኮኖሚክስ ምሁር ለግንቦት ሰባት ድምጽ በላኩት ጥናታዊ ጽሁፍ የወያኔ አገዛዝ ዉስጥ ዉስጡን የሚከተለዉ የገንዘብ ፖሊሲ የአገሪቱ አንጋፋ ባንክ የሆነዉን የእትዮጵያን ንግድ ባንክ እንደሚጎዳና በህወሀት አበላትና በቤተሰቦቻቸዉ የተያዙትን የግል ንግድ ባንኮች እንደሚጠቅም ለማወቅ ተችሏል።ይህ ጸረ አገር የሆነ የወያኔ ፖሊሲ የአገሪቱን የቁጠባ መጠን ከዚህ ቀደም ታይቶ ወደማይታወቅ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ማድረሱን እኚሁ አገር ወዳድ ምሁር የላኩልን ጥናታዊ መረጃ በግልጽ ያሳያል።

በቅርቡ አለምአቀፉ የገንዘብ ድርጅት ባወጣዉ መረጃ መሠረት ኢትዮጵያ ዉስጥ የህዝብም ሆነ የመንግስት ቁጠባ ያተኮረዉ በህዳሴዉ ግድብ ላይ ብቻ በመሆኑ አገሪቱ በካፒታል እጥረት የተነሳ ሌሎች ህዝብን የሚጠቅሙ ፕሮጀክቶችን ማስጀመርም ሆነ የተጀመሩትን ማስጨረስ አቅቷታል ብሏል። ይህ በአንድ አቅጣጫ ብቻ ያተኮረ የእንቨስትመንት ፖለሲ የአገሩቱ ባንኮች በተለይ አንጋፋዉ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በአገር ልማት ላይ ሊጫወት የሚችለዉን ትልቅ ሚና አሳንሶታል ሲሉ በዙ በግል ንግዱ ዘርፍ የተሰማሩ ነጋዴዎች በማጉረምረም ላይ መሆናቸዉ ታዉቋል።

በአጠቃላይ የወያኔ አገዘዝ እየተከተለ ያለዉ የገንዝብና የልማት ፖሊሲ የአገር ዉስጥ ባንኮችን የቁጠባ መጠን እጅግ በጣም ዝቅተኛ ደረጃ (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## ስብሐት ነጋ "የኢትዮጵያ ህዝብ ለድሞክራሲ ብቁ አይደለም" ሲል የጀርመን ሶሻል ዲሞክራሲ ፓርቲ ባዘጋጀው ስብሰባ ላይ መናገሩ በስብሰባው ላይ የተገኙትን ኢትዮጵያዊያን ማስቆጣቱ ታወቀ

ከዚህ ቀደም በተለያዩ መድረኮች ላይ ኢትዮጵያ ዉስጥ በግለሰቦች ላይ ሳይሆን በሂደት ላይ የተመሠረተ አስተማማኝ ዲሞክራሲ ገንብተናል ብሎ ይፎክር የነበረዉ ስብሐት ነጋ የጀርመን ሶሻል ዲሞክራሲ ፓርቲ በጠራዉ አለም አቀፍ ስብሰባ ላይ ተገኝቶ "የኢትዮጵያ ህዝብ ለዲሞክራሲ ብቁ አይደለም" በሎ በመናገሩን ስብሰባው ላይ የተገኙ ኢትዮጵያዊያንን እንዳስቆጣ በርሊን የሚገኘው የግንቦት ሰባት ተባባሪ ዘጋቢ በላከልን ሪፖርት ገለጸ።

በዚህ ኢትዮጵያን፤ ኬንያንና ማላዊን አንደዋነኛ ተጋባዥ አደርጎ ባሰተናገደ ስብሰባ ላይ ኢትዮጵያን ወክሎ የተገኘዉ ስብሐት ነጋ - በአንድ ሰዉ ሞት የተነሳ የድርጅት አላማ ሰለማይለወጥ በኢትዮጵያ መንግስት በኩል የፖሊሲ ለዉጥ አይኖርም ብሎ ከተናገረ በኋላ ንግግሩን ሲጨርስ "የኢትዮጵያ ህዝብ ለዲሞክራሲ ብቁ አይደለም" በሎ በመደምደሙ ዉይይቱን ለመከታተል አዳራሹ ዉስጥ ተገኝቶ የነበርው ቁጥሩ በዛ ያለ ኢትዮጵያዊ ቁጣውን በጩሄት በመግለጹ አስተናጋጆቹ እንደተደናገጡ ተያይዞ የደረሰን ዘገባ አመልክቶአል።

ስብሐት ነጋ አፉቸዉ እንዳመጣ ከሚዘላብዱና የኢትዮጵያን ህዝብ መሳደብ ከሚወዱ ወንጀለኛ የወያኔ መሪዎች አንዱ መሆኑ የሚታወቅ ቢሆንም የራሱን ጅልነትና ለህዝባችን ያለውን ንቀት በእንዲህ አይነት አለም አቀፍ መድረክ ላይ ይገልጻል ተብሎ እንዳልተጠበቀ በስብሰባው ላይ የተገኙ ኢትዮጵያዉያን ተናግረዋል። ስብሐት ነጋ ለህዝባችን ያለውን የንቀትና የእብሪት ንግግር ተናገሮ ሳይጨርስ በቁጣ ደማቸው የፈላ ኢትዮጵያዉያን ከመቀመጫቸዉ ብድግ ብለው ባንዳነቱንና በወያኔ የሥልጣን ዘመን ለተገደሉ ኢትዮጵያዊያን ተጠያቂ መሆኑን ጋባዦቹ ፊት በመናገር አዋርደውታል።

ስብሃት ነጋ ወያኔን በመምራት አገራችን ላይ ዘረኛ ሥርዓት እንዲነግስ ካደረጉ የህወሃት ቁንጮዎች አንዱ መሆኑን እየታወቀ ድህሬ መለስ ዜናዊ ኢትዮጵያ አገራችን ወዴት ልታመራ እንደምትችል ለጀርመን የምክር ቤት አባላት በኢትዮጵያ አለም አቀፍ የሰላምና የልማት ኢንስቲቲዩት በእንግሊዘኛው አጠራሩ Ethiopian International Institute for Peace and Development ሥም መጋበዙ በርካታ ኢትዮጵያዊያንና ስለ ኢትዮጵያ ጉዳይ የሚከታተሉ ጀርመናዊያንን አስገርሞአል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

# በወያኔ መዳፍ ውስጥ ያለችው ኢትዮጵያ በገለልተኛ ተቋማት ሚዛን

ዘረኛውና አምባገነኑ ወያኔ ሥልጣን ላይ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ኢትዮጵያ በሁሉም ዘርፎች በመመንጠቅ ላይ ያለች ለማስመሰል ይጥራል። ይባስ ብሎም በሌሎች አገራት እድገት የሌለ በማስመሰል ስለ መለስ ዜናዊ "ተዓምራዊ" አመራር ይደሰኩራል። በፍትህ፣ በዲሞክራሲና መልካም አስተዳደር ረገድም የሚደርስብኝ የለም እያለ ይፎክራል።

"ይሉሽን በሰማሽ ..." ለማለት ያህል ገለልተኛ የምርምር ተቋማት ስለኢትዮጵያ ካሉት ጥቂቶችን ለአብነት እናቅርብ።

**1. በአፍሪቃ የመልካም አስተዳደር መለኪያ /Mo Ibrahim Governance Index/**

"ሞይ ኢብራሂም ፋውዴሽን" በአፍሪቃ ውስጥ መልካም አስተዳደርን ለማበረታታት የተቋቋመ ግብረ-ሰናይ ድርጅት ነው። ከፋውንዴሽኑ ፕሮግራሞች አንዱ አገራቸውን በመልካም ሁኔታ አስተዳድረው የሥልጣን ሽግግር ላደረጉ የአፍሪቃ መሪዎች 5 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር በመሸለም መልካም አስተዳደርን ማበረታታት ነው። ይህ ፋዉንዴሽን ሥራውን ከጀመረ ስድስት ዓመታት ቢሞሉትም እስካሁን ለመሸለም የታደለው ግን ሶስት የአፍሪቃ መሪዎችን ብቻ ነው። እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ2007 የሞዛቢኩን ፕሬዚዳንት ጃኪም አልቤርቶ ቺሳኖ፣ በ2008 የቦትስዋናውን ፕሬዚዳንት ፌስተስ ጎንተባንዬ ሞጋዬ እና አምና በ 2011 የኬፕ ቨርዴውን ፕሬዚዳንት ፔድሮ ቬሮና ፓይረስ ይህን ታላቅ ሽልማት አግኝተዋል። ወያኔ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥንና አፍቃሪ ወያኔዎች "ታላቁ የአፍሪቃ መሪ" እያሉ የሚያሞካሹት ሰው መለስ ዜናዊ በዝርዝሩ ውስጥ ገብቶ እንደማያውቅ ልብ ይበሉ።

ፋውንዴሽኑ በየአመቱ የአፍሪቃ አገሮች በመልካም አስተዳደር ረገድ የደረሱበትን በመለካት "የሞይ ኢብራኢም የመልካም አስተዳደር ኢንዴክስ" የሚባል ደረጃ ያወጣላቸዋል። ይህ መለኪያ የሚከተሉት ዋና ዋና መመዘኛዎች አሉት፡ -

ሀ) ደህንነት እና የህግ የበላይነት፣
ለ) የሕዝብ ተሳትፎ እና የሰብዓዊ መብቶች መከበር፣
ሐ) ቀጣይነት ያለው ኢኮኖሚያዊ እድገት፣ እና
መ) ሰብዓዊ እድገት ናቸው።

አምሳ ሁለት የአፍሪቃ አገሮች በአለፈው የአውሮፓውያን ዓመት ያስመዘገቡት ውጤት ከላይ በተዘረዘሩት አራት መመዘኛዎች መሠረት ተገምግመው ያገኙት ደረጃ ሰሞኑን ይፋ ሆኗል። የመለስ ዜናዊዋ ኢትዮጵያ ከ52 አገሮች በአጠቃላይ ውጤት 46.7 ከመቶ በማግኘት 33ኛ ወጥታለች። በተለይም በፀጥታና በህግ የበላይነት እጅግ አሽቆልቁላ 38ኛ ደረጃ ላይ ወድቃለች። ከሁሉም የባሰው ደግሞ በሕዝብ ተሳትፎ እና ሰብዓዊ መብቶች አጠባበቅ ነው - በእነዚህ ኢትዮጵያ 39ኛ ሆና ከአፍሪቃም በመጨረሻዎቹ ተርታ ትገኛለች።

የወያኔ ዘረኛ አገዛዝ ይህችን ታላቅ አገርና ይህን ታላቅ ሕዝብ ከሌሎች የአፍሪቃ አገሮች ጋር ሲወዳደር ለእንዲህ ዓይነት ዝቅተኛ ውጤት እንደዳረጋት ልብ ይሏል።

**2. ዘርፈ-ብዙ የድህነት መለኪያ (Multidimensional Poverty Index)**

ዘርፈ-ብዙ የድህነት መለኪያ፣ በቤተሰብ ደረጃ ያለ የድህነት መጠንን በተለያዩ አቅጣጫዎች የሚለካበት መመዘኛ ነው። ምግብ፣ መጠለያ፣ የንጹህ ውሃ አቅርቦት፣ የማገዶ አቅርቦት፣ ህክምናና ትምህርት የመሳሰሉት ሁሉ በዚህ መመዘኛ የተካተቱ በመሆናቸው ድህነትን ለመለካት ከሌሎች መመዘኛዎች የተሻለ ነው ተብሎ ይታመናል።

የተባበሩት መንግሥታት የልማት መርሃግብር (ዩ.ኤን.ዲ.ፒ) ዘንድሮ ይፋ ባደረገው የጥናት ውጤት መሠረት 89 ከመቶው የኢትዮጵያ ቤተሰብ ድሃ ተብሎ የሚፈረጅ ነው። ቢሊየነር እና ሚሊየነር የሆኑ ወያኔዎችና አጫፋሪዎች መኖራቸው እውነት ቢሆንም የ89 በመቶው ሕዝቧ የቀን ገቢ ግን ከአንድ ዶላር ከሃያ አምስት ሣንቲም በታች ነው። ይህ ውጤት ኢትዮጵያን የዓለም ሁለተኛዋ ድሃ ያደርጋታል።

በዩ.ኤን.ዲ.ፒ መረጃ በኢትዮጵያ ውስጥ ማንበብና መፃፍ የሚችለው ሕዝብ 28 በመቶ ብቻ ነው። ይህ ውጤት ኢትዮጵያ አገራችንን በትምህርት ስርጭት ከዓለም ከመጨረሻ ሁለተኛ ያደርጋታል። ይህ ሁሉ የሚሆነው ወያኔ ትምህርትንና የጤና አገልግሎትን በማዳረስ የሚበልጠኝ የለም እያለ በሚፎክርበት አገር ውስጥ ነው።

**3. የኢኮኖሚ ነፃነት መለኪያ /Index of Economic Freedom/**

"ሄሪተጅ ፋውንዴሽን" በዓለም ላይ ያሉ አገሮችን ኢኮኖሚዎችን በጥልቀት በመመርመር የቱን ያህል ነፃ መሆናቸውን ይለካል። ይህ ጥናት በሥራ ላይ ከዋለ ከአስራ አምስት ዓመታት በላይ የሆነው ሲሆን ኢኮኖሚዎች ምን ያህል ወደ ገበያ ኢኮኖሚነት እየቀረቡ አለያም ከዚያ እየራቁ እንደሆነ በመለካት ረገድ አቻ ያልተገኘለት እና ሰፊ ተቀባይነት ያገኘ መመዘኛ ነው። ይህ መለኪያ የኢኮኖሚ ነፃነትን በአስር የኢኮኖሚ ነፃነት አይነቶች ከፋፍሎ ይገመግማል። እነዚህም ሀ) የቢዝነስ ነፃነት፣ ለ) የኢንቬስትመንት ነፃነት፣ ሐ) የንግድ ነፃነት፣ መ) የበጀት ነፃነት፣ ሠ) የፋይናንስ ነፃነት፣ ረ) የንብረት ነፃነት፣ ሰ) የመንግሥት ወጪ፣ ሸ) ከሙስና ነፃ መሆን፣ ቀ) የገንዘብ ነፃነት፣ እና በ) የሥራ ነፃነት ናቸው።
በያዝነው የአውሮፓውያን 2012፤ 179 አገሮች ደረጃ ወጥቶላቸዋል። ከዓለም ከሁሉም የተሻለ ነፃ ኢኮኖሚ ያላት አገር ሆንግ ኮንክ ስትሆን ያገኘቺው አጠቃላይ ነጥብ 89.9 ነው። ኢትዮጵያ ደግሞ 52.0 አጠቃላይ ነጥብ በማምጣት 134ኛ ደረጃ ይዛለች። ይህ አጠቃላይ ውጤት ኢትዮጵያን "ኢኮኖሚያቸው ባብዛኛው ነፃ ያልሆነ" ከሚባሉ አገሮች ጋር መድቧታል። ይህ የሚያመለክተው ወያኔ በኢትዮጵያ የገነባው የኢኮኖሚ ሥርዓትን የገበያ ኢኮኖሚ ነው ብሎ መጥራት የማይቻል መሆኑ ነው። አሁንም ለንጽጽር እንዲረዳን በአፍሪካ ደረጃ እንኳ ሩዋንዳ፣ ታንዛኒያ፣ ዛምቢያ፣ ኬኒያ፣ ማሊ፣ ሴኔጋል፣ ማላዊ እና ኮትዲቯር በኢኮኖሚ ነፃነት ከኢትዮጵያ በተሻለ ደረጃ ላይ ከሚገኙ በርካታ የአፍሪካ አገሮች ጥቂቶቹ ናቸው።

**4. የጨነገፉ መንግሥታት መለኪያ /Index of Failed States/**

"ዘ ፈንድ ፎር ፒስ" መንግሥታት ሕዝባቸውን በመምራት ረገድ ያሉባቸውን ድክመቶች በአስር ዋና ዋና መመዘኛዎች ይለካል።
እነዚህም
ሀ) ፈጣን የሕዝብ ብዛት የሚፈጥረው ውጥረት፣
ለ) የሕዝብ ከመኖሪያ ቦታው መፈናቀል፣
ሐ) የቡድኖች (የማኅበረሰብ) በሥርዓቱ መማረር፣
መ) ስደት፣
ሠ) አድሏዊ የሆነ ልማት፣
ረ) የኢኮኖሚ ድቀት፣
ሰ) የመንግሥት በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት ማጣት፣
ሸ) የመንግሥት አገልግሎት አናሳነት፣
ቀ) የፀጥታ ኃይሎች ብቃት ማነስ፣
በ) የፖለቲካ ልሂቃን የእርስ በርስ መቆራቆስ፣ እና
ተ) የውጭ ጣልቃ ገብነት ናቸው። ይህን ጥናት የሚያካሄደው የውጭ ፓሊሲና የሰላም ፈንድ የተባለ የምርምር ተቋም ሲሆን የምርምር ውጤቶቹ ከፍተኛ ዓለም ዓቀፍ ተቀባይነት ያላቸው ናቸው።

እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር የ2011፣ የ179 አገሮች ዓመታዊ ውጤት በቅርቡ ወጥቷል። ዘንድሮም በጨነገፉ መንግሥታት መለኪያ ዓለምን የምትመራው ጎረቤታችን ሶማሊያ ስትሆን ያገኘችው አጠቃላይ ነጥብ 114.9 ነው። ኢትዮጵያ በ97.9 በሆነ አጠቃላይ ነጥብ 17ኛ ደረጃ ይዛ በቅርብ እርቀት ትከተላታለች። ለማነፃፀር ያህል ዩጋንዳ፣ ስሪላንካ፣ ብሩንዲ፣ ላይቤሪያ፣ ሩዋንዳ እና ኤርትራ ከኢትዮጵያ የተሻለ አስተማማኝ መንግሥታት ያላቸው ሆነው ተገኝተዋል። እስከ ሠላሳ ሶስተኛ ተራ ቁጥር የተዘረዘሩት መንግሥታት "በመውደቅ ላይ ያሉ መንግሥታት" የሚል ስያሜ ተሰጥቷቸዋል። ይህ ስያሜ በእነዚህ አገራት ውስጥ መንግሥት አለ ለማለት አያስችልም የሚል መልዕክት አለው። ወያኔ ሰላምና መረጋጋት ፈጠርኩ ብሎ የሚመፃደቅባት ኢትዮጵያ በመውደቅ ላይ ካሉ መንግሥታት አንዷ እንደሆነች ተገልጿል። ትርጉሙም ኢትዮጵያ ውስጥ "መንግሥት" ለመባል የሚበቃ ተቋም የለም ማለት ነው።

ከላይ የተጠቀሱት ድርጅቶች የሚጠቀሙት የየአገሩ መንግሥታት የሚሰጧቸውን መረጃ ነው። ድርጅቶቹ እንዲህ ዓይነቱ መረጃ ላይ የደረሱት ባብዛኛው ራሱ ወያኔ በሚሰጣቸው መረጃዎች መነሻነት ነው።

ወያኔ መረጃዎችን እንደሚያዛባ ብዙ የተባለበት በመሆኑ እዚህ ላይ ማንሳት አያስፈልግም። የሚገርመው ግን እነዚያ የተዛቡ መረጃዎችን ይበልጥ አዛብቶ "የሚያነባቸው" መሆኑ ነው። ራሱ ወያኔ የሚያወጣቸውን መረጃዎች በጥንቃቄ ያነበበ ሰው የሚያስጨፍርና የሚያስፈነድቅ ነገር እንደሌለባቸው ይረዳል።

ወያኔ በቴሌቪዥንና ራድዮ ስለድልና ልማት ሲያደነቁረን በራሱ መረጃ መነሻነት የተሰሩትን የጥናት ውጤቶችን ይዘን "ይሉሽን በሰማሽ .." እያልን አገራችን ውስጥ እውነተኛ የኢኮኖሚ ዕድገት፤ ማኅበራዊ ፍትህና ዲሞክራሲ እንዲያብብ ሁላችንም እጅ ለእጅ ተያይዘን መታገል ይኖርብናል።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

## ስብሐት ነጋ "የኢትዮጵያ ህዝብ ለድሞክራሲ ብቁ አይደለም" ሲል የጀርመን ሶሻል ዲሞክራሲ . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

በጀርመን የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን የፖለቲካ አክቲቪስቶች የሶሻል ዲሞክራቲክ ፓርቲው ስብሃት ነጋንና ሞገስ ተክለሚካኤል የተባሉትን ቱባ ቱባ የወያኔ ባለሥልጣናት ህወሃት ውስጥ ያላቸውን የሃላፊነት ድርሻ እያወቀ ገለልተኛ አስመስሎ መጋበዙን በመቃወም ደብዳቤ ያስገቡ እንደሆነና ስለኢትጵያ መጻዕ እድል የሚያሳስበው ወዳጅ አገር እንዲህ አይነት ስህተት ይሰራል ተብሎ እንደማይጠበቅ መግለጻቸውን ለማወቅ ተችሎአል።

ባለፈው ጥቅምት 9 በርሊን ላይ የተደረገውን ስብሰባ የመሩት አንድ የጀርመን ምክር ቤት አባል ይህንን ስብሰባ የጠራነዉ ኢትዮጵያ ዉስጥ ከመለስ ዜናዊ ሞት በኋላ ሊኖር የሚችለዉን ለዉጥ ለማወቅ ነበር፤ ሆኖም የኢትዮጵያው ተወካይ ምንም አይነት የፖሊሲ ለዉጥ አይኖረም በማለታቸዉ ኢትዮጵያን የሚመለከተዉ አጀንዳ ተዘግቷል በማለት ተስፋ መቁረጣቸውን ፊትለፊት ገልጸዋል።

## ኃይለማርያም ከመድረሱ፤ የንፁሃንን ሕይወት መቀንጠሱ!!!

### የግንቦት 7 መግለጫ

ኃይለማርያም ደሣለኝ ምስለኔ ነው። ዋናው ባለሥልጣን ገና በውል አልታወቀም። ለሽያጭ ገበያ እንደወጣ ፈረስ ተስፈኛ ገዢዎች ኃይለማርያምን ለሙከራ እየጋለቡት ነው። በእርግጠኝነት የሚታወቀው ኃይለማርያም ደሣለኝ ምስለኔ እንጂ ዋናው ባለሥልጣን አለመሆኑ ብቻ ነው። እሱም ይህን ተቀብሎታል። የኃይለማርያም አዲስ ጌታ ነጥሮ ባለመውጣቱ ከቀድሞ ጌታው የተረከባቸውን ሹማምንት ይዞ ይቀጥል ወይም ጥቂት ለውጦችን ያድርግ ለጊዜው በውል የሚታወቅ ነገር የለም። ምን ያህል ሥልጣን በእጁ እንዳለም እንኳንስ ሌላው ሰው እሱም አያውቀውም። የመኖሪያ ቤትም ስላልተለቀቀለት ገና ወደ ቤተመንግሥት አልገባም።

እንዲህ ብዙ ነገሮች ገና ያልለየላቸው ቢሆንም ኃይለማርያም የቀድሞ ጌታው የመለስ ዜናዊን "ሌጋሲ" ለማስፈፀም ሲል ከአሁኑ ኢትዮጵያዊያንን መግደል ጀምሯል።

ለካስ ኢትዮጵያዊያንን በግፍ መጨፍጨፍ ነበር ኃይለማርያም ደሣለኝ ገና ከጠዋቱ ደጋግሞ "የኔ ሥራ የታላቁ መሪያችንን ሌጋሲ ማስቀጠል ነው" ሲል የነበረው!! እንዳለውም "የመሪውን ሊጋሲ" የሚያስቀጥል መሆኑን ከጅምሩ አሳየን።

የኃይለማርያም ደሣለኝ የምስለኔ አገዛዝ የመጀመሪያ ሰለባዎች ሙስሊም ምዕመናን ሆኑ። ቀኑም እሁድ ጥቅምት 11 ቀን 2005 ዓ.ም. ነበር። በደቡብ ወሎ በምትገኘው ገርባ ከተማ የሚገኙ ሙስሊም ምዕመናን በሣምንታት በፊት በተካሄደው የውሸት ምርጫ ባለመሳተፋቸው ሰበብ ተፈልጎ የጥይት ዝናብ ወረደባቸው። ምዕመናኑ በመስጊዳቸው ለመጠለል ሞከሩ፤ ግን አልቻሉም። የፖሊስ ልብስ የለበሱ የጦር ሠራዊት አባላት ምዕመናኑን በጭስ አፍነው በጥይት ቆሏቸው። እስካሁን ከአራት ያላነሱ ሰዎች ሕይወታቸውን ማጣታቸው ተረጋግጧል። የሟቾች ብዛት ከዚህም በላይ እንደሚሆን ይገመታል። ከአንድ መቶ በላይ የሚሆኑ ሰዎች ለአካል ጉዳት ተዳርገዋል። ጥቂቶቹ ደሴ ሆስፒታል ተወስደው የህክምና ርዳታ ያገኙ ቢሆኑም ብዙዎች ግን ይህንን እድል አላገኙም።

የኃይለማርያም የምስለኔ አገዛዝ አንድ ፓሊስ ተገድሎብኛል ቢልም እውነት ይሁን አይሁን እስካሁን ማረጋገጥ አልተቻለም። የቀድሞ ጌታው መለስ ዜናዊ ሰው በገደለ ቁጥር "ፓሊስ ተገድሎብኛል" ይል እንደነበረው ኃይለማርያምም ተመሳሳይ ውሸት መፈብረክ "የሌጋሲው" አካል አድርጎት ሊሆን ይችላል፤ ለጊዜው እርግጠኛው አልታወቀም።

በእርግጠኝነት የሚታወቀው ነገር በጥቅምት 11 ቀን 2005 ዓ.ም. በገርባ ከተማ ከአንድ መቶ በላይ በሆኑ ንጹሃን ዜጎች ላይ የሕይወት መጥፋት ወይም የአካል ጉዳት ያስከተለ ግፍ መፈጸሙ ነው።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በወገኖቻችን ላይ በደረሰው ጭፍጨፋ የተሰማውን ጥልቅ ሃዘን ይገልፃል፤ ለሟቾቹ ገነትን ለቤተሰቦቻቸው ደግሞ መጽናናትን ይመኛል። ግንቦት 7 እነዚህ ውድ ኢትዮጵያዊያን ለመብቶቻቸው መከበር ሲሉ ከፍተኛውን የሕይወት መስዋትነት የከፈሉ ሰማዕታት አድርጎ ይመለከታል።

ኃይለማርያም ደሣለኝ፣ እውነተኛ ሥልጣን ኖረውም አልኖረው ለወያኔ በምስለኔነት ለመሥራት ፈቅዶና ወዶ ገብቶበታልና በወገኖቻችን ደም ቀጥታ ተጠያቂ ነው ብሎ ግንቦት 7 ያምናል። የይስሙላም ቢሆን ገና በሥልጣን ወንበር ላይ እንደተቀመጠ የንጹሃንን ደም ማፍሰሱ ኃይለማርያምን ልክ እንደ ቀድሞ ጌታው መለስ ዜናዊ ፀረ-ሕዝብና ፀረ-ኢትዮጵያ ያደርገዋል።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ፣ የወያኔ ዘረኛና አምባገነን ሥርዓት ለሰብዓዊ መብቶች ግድ ይኖረዋል ብለን አያምንም። ወያኔ ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ግድ እንዲኖረው ሊቋቋመው በማይችለው ኃይል መገደድ ይኖርበታል አሊያም ጭራሹን ሊወገድ ይገባል።

ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች እስካሁን በሰላማዊ መንገድ ወያኔ ለማስገንዘብና ለማንቃት ያደረጉትን ተጋድሎ ግንቦት 7 ያደንቃል። ከእንግዲህ ግን የማስገደዱ አለያም የማስወገዱን ሥራ በተቀናጀ መንገድ ካልሰራነው በስተቀር የሕዝባችን መገደል፣ መደብደብና መረገጥን ማስቆም አንችልም። ስለሆነም ግንቦት 7፣ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ - ሙስሊሙም ክርስቲያኑም - ለሰብዓዊ መብቶታችን መከበር በጋራ እንዲነሳ ጥሪ ያደርጋል።

በዚህ አጋጣሚም ክርስቲያኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሙስሊም ወንድሞቹና እህቶቹን ጥረት በጥርጣሬ መመልከቱን ትቶ ለጋራ ድል በጋራ እንዲነሳ ግንቦት 7 ጥሪ ያደርጋል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

---

## የዘንድሮው ኢድ አል አደሃ በአል የሙስሊሙ ህብረተሰብ . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ወያኔ ሙስሊሙን አስገድዶ በቀበሌ ያካሄደው የሰሞኑ ምርጫም ህጋዊ አይደለም የሚል መፈክር በስፋት የተደመጠ ሲሆን አህባሽ አይመራንም፤ የታሰሩት ወገኖቻችን ተወካዮቻችን እንጂ ሽብርተኞች አይደሉም የሚሉና በአስቸኳይ እንዲፈቱ የሚጠይቅ መፈክሮችም በሰፊው ተደምጠዋል።

ከአዲስ አበባ ከተማ ውጪ በሀረር፣ በደሴ፣ በአዳማ፤ በጂማ እና ሌሎችም ትላልቅ ከተሞች በተካሄደው ስነ ሥር ዓት ተመሳሳይ የሆነ ተቃውሞ መሰማቱን የገለጹ ምንጮች በዘንድርው የኢድ በአል ላይ የሃይማኖት መሪዎችም ሆኑ የመንግሥት ተወካዮች ቀርበው ንግግር እንኳ ለማድረግ ድፍረት እንዳጡ መስተዋሉን ገልጸዋል።

ግንቦት 7 የሙስሊሙ ህብረተሰብ ያነሳው የመብት ጥያቄ አይነት በኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንም ውስጥ ለረጅም ጊዜ ሰሚ አጥቶ ተዳፍኖ የኖረ መሆኑን በማመልከት አገራችን ውስጥ የዜጎችን መብት ማክበር የሚችል መንግሥት እስካልተቋቋመ ድረስ ከእንዲህ አይነት የወያኔ ጥቃት የሚተርፍ እንደሌለ በማመልከት ህዝቡ ለራሱ ነጻነት የተጀመረውን ትግል እንዲቀላቀል ጥሪ ሲያደርግ መቆየቱ አይዘነጋም።

---

## ወያኔ/ኢህአደግ ውስጥ የተፈጠረው ክፍፍል ግንባሩን ከማዳከም አልፎ . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

መከፋፈል መደበቅ ከማይቻልበት ደረጃ ላይ መድረሱን አረጋግጦአል።

ወያኔ / ኢህአዴግ ዛሬ ከላይ እስከ ታች በሙስና ተጨማለቋል፤ ይህ ድርጅቱን አበስብሶ የሚገድለው ነው ያለው ጋዜጣው፣ ሙሰኞቹ ባለስልጣናት ደግሞ አቅመ ቢስና ምላሰ ብዙ ናቸው፤ ምክንያቱም በወያኔ መንግስት ውስጥ በብቃት መመደብ እየቀረና አቅም ባይኖረውም ደጋፊ እስከ ሆነ ድረስ ችግር የለም በሚል የሚመደብ መሆኑ ነው።እናም ሁኔታው ህዝብ በወያኔ መንግስት ላይ አመኔታ እንዳይኖረው አድርጓል ሲል አስረድቷል።

እንደ ጋዜጣው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ የሚባለውም ከእቅድ አልፎ በይዘት እየተተገበረ አይደለም፤እንዳውም በብዙ ቦታዎች በእቅዱ ስም ገንዘብና ንብረት እየተዘረፈ ነው በማለት የወያኔ ቱባ ባለሥልጣናት ስለ ትራንስፎርመሽኑ ስኬታማነት የሚለፍፉትን ርካሽ ፕሮፖጋንዳ ባዶ መሆኑን አጋልጦአል።

ወያኔ ላለፉት 21 አመታት በአገሪቱ ፍትህና እኩልነት አሰፍኛለሁ በማለት የሚነዛውን ውሼት ዋጋ ብስነት በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ያጋለጠው ሪፖርተር "በፍትህ ረገድም ምንም ተስፋ የለም። ፍትህ ጨርሶ ጠፍቷል።ህዝብ አቤት የሚልበት ቦታ የለውም። የሚያነጋግረው ሹምም የለም "በማለት ድርጅቱ በአስተዳደር በደልና በንቅዜት ወደ መጨረሻው ግባተ መሬቱ እያመራ መሆኑን በማስጠንቀቂያነት መልክ ይፋ አድርጎአል።

## ኢትዮጵያ ዉስጥ ለተፈጠረዉ ከፍተኛ የቁጠባ እጥረት ዋናዉ ምክንያት . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ይህንን አገዛዙ እራሱ ሆን ብሎ የፈጠረዉን አደገኛ አዝማሚያ ለማስተካከል መንግስት በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ላይ ተጽዕኖ ማድረግ መጀመሩንና ጅምሩ የባንኩን ባለስልጣኖችና ሠራተኖች እያበሳጨ መሆኑን የአገር ዉስጥ ምንጮቻችን ተናግረዋል።

በዚህ መንግስት በቀየሰዉ የማስተካከያ ፖሊሲ መሠረት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ህብረተሰቡ ዉስጥ እየገባ ከእጅ ወደ አፍ የሚኖረዉን ገበሬና ሠራተኛ የቁጠባ መጠናችሁን ጨምሩ እያለ ማስጨነቅ መጀመሩን ከብዙ የአገሪቱ የገጠር አካባቢዎች የሚደርሱን ዜናዎች ያስረዳሉ። በተለይ ሰሞኑን ከአዲስ አበባ በደረሱን ዜናዎች መሠረት ይህ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ላይ ያተኮረዉ ህብረተሰቡን የማስጨነቅ ስራ በወያኔ ባለኃብቶች ቁጥጥር ስር የሚገኙትን የንግድ ባንኮች እንደማይመለከት ለማወቅ ተችሏል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በህወሀት ባለስልጣኖችና በቤተሰቦቻቸዉ ቁጥጥር ስር የሚገኙት ባንኮች ወያኔ የፈጠረላቸዉን መንገድ በመጠቀም ከብሔራዊ ባንክና ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ብዛት ያለዉ ገንዘብ ተበድረዉ የዉጭ ምንዛሪ በመግዛት በቅርቡ ኢትዮጵያ ዉስጥ ለተፈጠረዉ የዉጭ ምንዛሪ እጥረት ምክንያት ሆነዋል። በቅርቡ ሀይለማሪያም ደሳለኝ ለፓርላማዉ በሰጠዉ መግለጫ የዉጭ ምንዛሪ ችግር የለብንም ብሎ የጌቶቹን ዝረፊያ ለመደበቅ ቢሞክርም የወያኔ ባንኮች የሚሰሩት ስራ በአንድ በኩል የአገሪቱን የዉጭ ምንዛሪ ክምችት ከፍተኛ አደጋ ላይ የጣለዉ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የአገሪቱን የብድር ካፒታል ልማታዊ ላልሆነ ስራ በመጠቀም የአገር ዉስጥ ባለኃብቶችን እንቅስቃሴ ያደከመ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

---

## የከሚሴ ከተማ የጦር ሜደ መሳሪያ ባነገቡ የፌዴራል ፖሊስ አባላት ተወረረች - ደቡብ ወሎ ዉስጥ ዉጥረቱ ከቀን ወደ ቀን እየተባባሰ መምጣቱ ታወቀ

ባለፈዉ እሁድ የማምለክ መብታቸዉ እንዲከበር በሠላማዊ መንገድ ጥያቄ ባቀረቡ የእስልምና እምነት ተከታይ ዜጎች ላይ ተኩስ በመክፈት አራት ዜጎችን በግፍ የገደሉት የወያኔ ልዩ የጸጥታ ኃይሎች የሽብር ተግባራቸዉን በማስፋፋት የከሚሴን ከተማ ከብበዉ የከተማዋን ነዋሪ ህዝብ በማሸበር ላይ መሆናቸዉን ዝግጅት ክፍላችን ድረስ ስልክ እየደወሉ የድረሱልን ጥሪ ያቀረቡት የከሚሴ ከተማና የአካባባዉ ነዋሪዎች ገለጹ።

ይህ በያዝነዉ ሳምንት መጀመሪያ ላይ በአማራ ክልል ቃሉ ወረዳ ገርባ ቀበሌ ዉስጥ የወያኔ ታጣቂዎች የጀመሩት የሽብር እንቅስቃሴ በፍጥነት ወደሌሎች አካባቢዎች በመስፋፋት ላይ መሆኑንና ነዋሪዉ ህዝብ ከተማዉን እየለቀቀ በብዛት ወደ ገጠር በመግባት ላይ መሆኑን ሁኔታዉን በቅርበት የሚከታተሉት የኢትዮጵያ ሳታላይት ዘጋቢዎች መግለጻቸውን ኢሳት ዘግቦአል።

እንደ ኢሳት ዘገባ ከፌዴራል ፖሊስ ከበባ አምልጠዉ በየጫካዉ ከተሸሸጉት ወጣቶች ዉስጥ አንዳንዶቹ ለዜና ማሰራጫው ስልክ በመደወል የከሚሴ ከተማ ብዛት ባላቸው የታጠቁ የወያኔ ፖሊሶች ስር መዉደቋንና ከቤት ወደ ቤት አሰሳ በማድረግ ወጣቶችን በማደን ተግባር መጠመዳቸውን አጋልጠዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸዉ የወያኔ መከላከያ ሠራዊትና የፌዴራል ፖሊስ አባላትን የጫኑ ካሚዮኖች በከሚሴና በደሴ አካባቢ በብዛት መታየታቸዉ የአካባቢዉን ህዝብ ክፉኛ እንዳስደነገጠዉ ለማወቅ ተችሏል። የዝግጅት ክፍላችን ከደሴ በስልክ ያናገራቸዉ አንድ አባወራ ወያኔ ጥያቄዎቻችንን የሚመለስዉ በጠመንጃ ብቻ ስለሆነ ልጆቻችንን ሊገድል ይችላል ብለን ብንሰጋም የወታደር ክምችትና የመሳሪያ ጋጋታ ለመብታችን ከመታገልና ጥያቄዎቻችንን ከማቅረብ በፍጹም አያግደንም ብለዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ መኖሪያ ቤቱ በፌዴራል ፖሊስ አባላት ሲከበብ በጓሮ በር ሸሽቶ ያመለጠ አንድ የከሚሴ ከተማ ነዋሪ ወጣት መንግስት ይዞ ያሰራቸዉን የመፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ አመራር አባላትን አስካልፈታና የሙስሊሙን ህብረተሰብ የማምለክ መብት እስካላከበረ ድረስ ትግላችን ይቀጥላል ካለ በኋላ የሰሞኑ እስርና የግፍ ግድያ የብዙ አለም አቀፍ የዜና አዉታሮች አይን መሳቡና አለም አቀፍ ሽፋን ማግኘቱ እጅግ በጣም እንዳስደሰተዉ ተናግሯል።

## ዘረኛውንና አምባገነኑን መለስ ዜናዊን የተካው ሃይለማሪያም ደሳለኝ የወያኔን የአፈና ተግባር አጠናክሮ እንደ ቀጠለ ፍኖተ ነጻነት ጋዜጣ ዘገበ

መለስ ዜናዊ የገነባው ስርዓት አብሮት እንዲቀበር የነፃነት ናፋቂ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ ምኞት ነበር፤ ይሁንና የመለስ ሞት የመንግስቱን ስልታዊ አምባገነንነት ቀመር በማሳጣቱ አሁን ያሉት አምባገነኖች ያፈጠጠና ያገጠጠ የአፈና ተግባር ውስጥ ገብተዋል ሲል ከወር እገዳ ቦኋላ ወደ ህትመት የተመለሰው የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) ልሳን ፍኖተ ነጻነት ጋዜጣ ገለጸ።

ፍኖተ ነጻነት እንዳለው አዲስ ተብዬው ጠቅላይ ሚኒስትርም በመለስ ሙት መንፈስ የሚመራ መንግስቱም ያው በመሆኑ በኢትዮጵያ አንጻራዊ የሚባል እንኳን ለውጥ ማየት አልተቻለም። ይልቁንም መንግስቱ ስራውን፣ ስርዓቱን የሚተቹ ጋዜጦችን ከአደባባይ በማጥፋት ነው የጀመረው።

እናም ስርዓቱ ለሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ይበለጥ ጸር እየሆነ መምጣቱ የትግሉን መንፈስን የሚያጠናክር እንጂ ተስፋ አስቆራጭ ሊሆን እንደማይችል በተለያዩ ሰላማዊ የመብት ማስከበሪያ ትግሎች ለወያኔ እንደሚያረጋግጡለት ያመላከተው ጋዜጣው እንዲህ ዓይነቱን ስርዓት የሚሸከም ጫንቃ እንደሌላቸውም በአጽንኦት አስረድቷል ።

በማከልም በጋዜጣው የሚንፀባረቁት የነፃነት ጥያቄዎች የህዝብ መሆናቸውን ያስገነዘበው ፍኖተ ነፃነት፣ ጋዜጣን በማፈን የህዝብን የለውጥ ፍላጐት ማፈን እንደማይቻል ስርአቱ በሚገባው ቋንቋ ሊነገረው ይገባል ብሏል።

በተለይም ራሱ የሚለውን እንደገደል ማሚቶ የሚያስተጋቡ አድርባይነትን ዋንኛ ተግባራቸው ያደረጉና ከስርአቱ በተለያየ ደረጃ የሚጠቀሙ ሆድአደር የመገናኛ ብዙሃንን በመደገፍ፤ በአንፃሩ ለህዝብ አማራጭ በመሆን በስርዓቱ ላይ ትችት የሚያሰሙትን መርጦ ማፈንና ማዳከም ውጤቱ ለወያኔ አደገኛ እንደሚሆን አስጠንቅቋል።

በማያያዝም የአንድነት እምነት በሀገራችን የተረገጡት መብቶች እንዲከበሩ ሁነኛው መፍትሄ ኢትዮጵያን በአፈና ቀንበር ስር ያደረገውን አምባገነን ስርዓት ማስወገድ መሆኑን ገልጾ ለዚህ ደግሞ ድርጅቱ በሚያስተባብራቸው ሰላማዊ የትግል እንቅስቃሴዎች በመሳተፍ ሁሉን አቀፍ የመብት ማስከበር ትግል ማድረግ አማራጭ እንደሌለው አብራርቷል።

በመጨረሻም የመለስን ሞት ተከትሎ በጋዜጣው አዘጋጅና በጋዜጠኞቹ ላይ የተፈጸሙትን ከግድያ ሙከራ እስከ ማስፈራራት ድረስ የነበሩትን የወያኔን ስርዓት እኩይ ተግባራት የጠቀሰው ፍኖተ ነጻነት መቼም ቢሆን በፍራቻ የሚነጥፍ ብእርም ሆነ በአፈና የሚንበረከክ ማንነት እንደሌላቸው አስረግጦ ተናግሯል።

## የወያኔ ፈደራል ፖሊስ በደቡብ ወሎ ዞን አራት ንጹሃንን ገድሎ በርካቶችን ማቁሰሉ ተዘገበ

ከትናንት በስቲያ ዕሁድ ጥቅምት 11 ቀን 2005 ዓም በደቡብ ወሎ ዞን በገርባ ቀበሌ ህዝብና በፖሊስ መካከል በተፈጠረው ግጭት 4 ሰላማዊ ዜጎች ከፖልስ በተተኮሰ ጥይት መገደላቸውን የግንቦት 7 ዘጋቢ ከስፍራው በላከልን ዘገባ ገለጸ።

በፖልስና በህዝቡ መካከል ለተከሰተው ግጭት መንስዔው ወያኔ ባለፈው ሳምንት በቀበሌ ጽ/ቤት እንዲካሄድ ያደረገው የሙስሊም ሃይማኖት መሪዎችን ምርጫ ተከትሎ በተፈጠረው ተቃውሞ ሁለት የቀበሌው ወጣቶች አክራሪ ናቸው በሚል የፈጠራ ክስ እንዲታሰሩ መደረጋቸው ነው ተብሎአል።

የገርባ ቀበሌ ህዝብ የታሰሩት እስረኞች እንዲፈቱለት በሰላማዊ መንገድ ለመጠየቅ ያደረገውን ጥረት ፖልስ በተለመደው የሃይል እርምጃ ለመበተን በመሞከሩ ሁለት ሰዎች ከፖልስ በተተኮሰ ጥይት ወዲያው ህይወታቸው እንዳለፈ ሌሎች ሁለቱ ደግሞ በፖልስ ቁጥጥር ሥር ከዋሉ ቦኋላ ራቅ ወዳለ ቦታ ተወስደው እንደተረሸኑ የደረሰን ዘገባ ያመለክታል።

በፖልስ ቁጥጥር ሥር ከዋሉ ቦኋላ ወደ ባቲ ይወሰዳሉ በሚል ሰበብ ከአካባቢያቸው ራቅ ወዳለ ቦታ ተወሰደው የተረሸኑት የሼህ ሁሴን እና አቶ ሰይድ አብደላን አስከሬን የተገኘው በገርባና በባቲ መካከል በምትገኘው ዱሪ ከተማ ላይ እንደሆነ ለማወቅ ተችሎአል።

ፖልስ በወሰደው እርምጃ የተቆጣው የገርባ ቀበሌ ህዝብ በወሰደው አጸፋ እርምጃ ሁለት የፌደራል ፖሊስ አባላት በገጀራና በድንጋይ ተደብድበው መገደላቸውን ተያይዞ የደረሰን ዘገባ ያመለክታል።

ሃይለማሪያም ደሳለኝ ሥልጣን ላይ በመጣ ወር በማይሞላ ጊዜ ውስጥ የተወሰደው ይህ ጨቃኝ እርምጃ የሚያሳየው ነገር ቢኖር ወያኔ የወኪሎቹን መልክና ብሄረሰብ ይቀይር እንደሆን እንጂ ጸረ ህዝብና ጸረ አገር ተግባሩን ይቀይራል ተብሎእ እንደማይታሰብ ማረጋገጫ ሆኖአል።

አድማጮቻችን የግንቦት 7 ንቅናቄ ይህንን የወያኔ ግዲያ አስመልክቶ ያወጣውን መግለጫ ከዜናው ቀጥሎ የምናቀርብ መሆናችንን እንገልጻለን።

## በኢትዮጵያ ቃላት ሰማይ ተግባር ገደል ሆነው አልጣጣም ብለዋል፤ ህገ መንግስትና ህጎች በወረቀት ላይ አሉ በተግባር ግን ደካማ ናቸው ሲል አፍቃሪ ወያኔው ሪፖርተር ገለጸ

የወያኔ ስርዓት ወደማይቀረው ሞቱ በፍጥነት እየገሰገሰ መሆኑን ያጤነው የጋዜጣው አዘጋጅ በዚሁ ጽሁፉቢያንስ ለትንሽ ጊዜ እድሜውን እንዲያራዝም አንዳንድ በግድ መሻሻል አለባቸው ያላቸውን ጉዳዮች አንስቷል።

ጋዜጣው ባነሳው ያፈጠጠ እውነታ ህጎች ይወጣሉ በተገቢው መንገድ አይተገበሩም። ዜጎች በእኩልነት አይታዩም፣ የማይፈለጉ ተጠያቂ ይደረጋሉ ሌሎች እንዳሻቸው ይፈነጫሉ። ሌቦች እኩል አይቀጡም፤የሚያነባውና እንባ ጠባቂው አብረው መጓዝ አልቻሉም። ፍትህ እንደ ሰው እንጂ እንደ ህጉ አይሰጥም።በጥቅሉ የፍትህና የህግ ተቋማት የግለሰቦች ምስል እንጂ የህገ-መንግስትና የህግ አለኝታ ተቋማት አይደሉም በማለት አብራርቷል።

ጋዜጣው አያይዞም በሚዲያ አፈና፣ ሲቪል ማህበረሰብን በማዳከም፣ ሰብዓዊመብት በመጣስ፣አበረታች የኢንቨስትመንት ፖሊሲ ባለማውጣትና የተሳካ ምርጫ ባለማካሄድ ከፍተኛ ችግር እንዳለና በዓለምአቀፉ ማህበረሰብ ዘንድም የተወገዘች ሀገር መሆኑዋን ይፋ በማድረግ በአለምአቀፉ ማህበረሰብ ዘንድ በእጅጉ የተደነቅን ነን የሚለውን ወያኔያዊ አደንቋሪ ጩኸት በመተው ከእውነታው ጋር እንዲጋፈጡ አሳስቧል።

በማከልም የወያኔ መንግስት ሙስናን በቃል እንጂ በተግባር እንደማይዋጋ ገልጾ በሙስና ተጨማልቀው መልካም አስተዳደር እንዳይኖር የሚያደርጉና የፍትህን ክብር የሚያዋርዱ ሹማምንትን ህዝብ ፈጽሞ አይፈልጋቸው በማለት የወያኔ ስርዓት አደጋ ላይ መሆኑን ጠቁሟል።ከዚህም ሌላ ህዝቡ በኑሮው የወሬ ሳይሆን ተጨባጭ ለውጥ ማየት እንደሚፈልግ በማንሳት አሁን ያሉት እውነታዎች ግን የወያኔ ሚዲያዎች እንደሚደሰኩሩት ሳይሆን የኑሮ ውድነት፣ ግሽበት፣ የውጪ ምንዛሪ እጥረት፣ የባንኮች ብድር መከልከልና የመሳሰሉት ችግሮች መሆናቸውን አስምሮበታል። በመጨረሻም የኢትዮጵያ ተጨባጭ እውነታ የመለስን ራእይ በተግባር እናውላለን እያሉ፣ ያለፈውን እየተረኩ ባለህበት ሂድ የሚባልበት ሳይሆን አዳዲስ ለውጦችን ለማምጣት መንቀሳቀስን የሚጠይቅ መሆኑን በማስረገጥ የመለስ ሌጋሲ እያሉ ለሚያላዝኑት መናጀ ባለስልጣናት ማስጠንቀቂያ ሰጥቷል።

### የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz

<u>አጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz

**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**

**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org